የሰበር መ/ቁ. 21816

ቀን ሚያዝያ 04/1998 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** የአምቦ ማዕድን ውሃ ፋብሪካ

**ተጠሪዎች፡-** እነ አብዮት ኢዴቲ /48 ሠዎች/

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /Cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? ጉዳዩንስ ለመዳኘት የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የህግ ነጥብ የሚመለከት ነው፡፡

የም/ኦሮሚያ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ በመቀበል አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ከላይ የተመለከተውን የህግ ነጥብ ሳይመረመር አልፎታል፡፡

አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪ/ዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 11\9\98

ችሎቱም ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የህግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ መርምሯል።

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 16273 ጥቅምት 22 ቀን 1998 በሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የህጉን ድንጋጌዎች በመተርጎም አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከአሰሪና ሠራተኛ ሕጉ አንፃር ሊያገኘው የሚገባና የቀረበት ጥቅም ካለ የቀረበት ጥቅም እንዲሰጠው መጠየቅ /ክስ ማቅረብ/ የሚችል ሲሆን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ በሚል ብቻ የሚቀርብን ክስ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድም ሆነ የሥራ ክርክር ችሎት ተቀብለው ሊያዩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

በሌላም በኩል ቢሆን በመ/ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመተርጎም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የሥራ ጉዳዮችን ነው። አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። በአንፃሩ አንድ የሥራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራከረው ሠራተኛ /ሠራተኞች/ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሲገኝ ነው በማለት የህግ ትርጉም ሰጥቷል።

በዚህ ጉዳይም የም/ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ/ዎች ያቀረቡት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ የክስ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 11/9/98

ምክንያት የሌለው ከመሆኑም በአሻገር የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ምክንያቶች የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባው ጉዳዩን አከራክሮ በመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

- የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ.ቁ. ___ በግንቦት 26 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30086 በሐምሌ 04 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ — [signature] ቀን 11/9/98